## የዲሲ ሰብዓዊ መብቶች ማስርያ ቤት(D.C. Office of Human Rights (OHR)
## የደንበኞችን ባህሪን ( Conduct) በተመለከተ የወጣ መመርያ

**ፌብሩዋሪ 2026**

### ክልል/ወሰን

ይህ መመርያ ሁሉንም ዓይነት የግንኙነት መንገዶችን የሚያጠቃልል ነው። በአካልም ይሁን በስልክ፣ በኢሜልም ሆነ በቨርችዋል (virtual) ስብሰባዎች ወይም በጽሁፍ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በሙሉ ይመለከታል። ይህም ደንበኞችንና የኦ ኤች አር (OHR) ሰራተኞች፣ኮንትራክተሮች ወይም ካለ ክፍያ የሚሰሩ በጎ አድራጊ ሰራተኞች ወይም በስልጠና ላይ ያሉ ጀማሪ ሰራተኞችን በሙሉ ይመለከታል። በተጨማሪም መመርያው ጠበቃዎችንና ጠበቃ ያልሆኑ ወኪሎችን እንዲሁም ወደ መስርያ ቤታችን የሚመጡ ቡድኖችንም ይመለከታል።

### የሚጠበቅ ጠባይ

ኦ ኤች አር (OHR)፤ ለደንበኞቹም ሆነ ለሰራተኞቹ፤ የሰውን ክብር የሚጠብቅ፣ ሙሉ በሙሉ ሞያዊ የሆነና ሰላም የተመላበት አገልግሎት ለመስጠት ቁርጠኛነቱን ይገልጻል። ደንበኞቹም ማንኛውንም እንቅስቃሴ በሚያከናውኑበት ወቅት የሚከተሉትን ባህርያት እንዲያሟሉ ይጠብቃል።

ደንበኞቻችን በሚከተሉት ጠባዮች እንዲገዙ እንጠይቃለን፤

- ሰራተኞችን በከበሬታና በኣክብሮት እንዲይዙ
- ግንኙነት ሲያደርጉ በተረጋጋ መንፈስና ሞያዊ በሆነ መንገድ እንዲሆን
- በኦ ኤች አር (OHR) መስርያ ቤት ክልል ውስጥ ባሉበት ግዜና ኦፊሲያላዊ ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት፤ የመስርያ ቤቱን መመርያዎች እንዲከተሉ

### ተቀባይነት የሌለው ባህሪ

**የሚከተሉት ጠባዮች** የተከለከሉ ናቸው፤

- **በንግግር የሰውን መብት መግፈፍ (Verbal abuse)፤** በሰው ላይ መጮህ፤ ስድብ መሳደብ፣ ዛቻ ወይም ጸያፍ ቋንቋ መጠቀም
- **ሰውን ማጉላላት ወይም አድልዎ ማድረግ (Harassment፣ discrimination)፤** ዘርን፣ ጾታን፣ ወይም የጾታ ማንነትን፣ አካል ጉዳተኝነትን፣ ብሄራዊ አመጣጥን/ማን ነትን /ወይም የሆነ በዲሲ ህግ የተከለከለ ባህርይን በማሳየት ተጽ እኖ ማድረግ
- **የጠብ አጫሪ ጠባይ፤** ዛቻ ወይም አስጸያፊ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ በሌላ ሰው ላይ ያልተፈለገ አካል መነካካት ማድረግ፤ ቁሳቁሶችን መወርወር
- **የጦር መሳርያ፤** መሳርያ አውጥቶ ማሳየት፣ መሳርያ መጠቀም ወይም በመሳርያ ሰውን ማስፈራራት
- **በመስርያ ቤቱ መመርያዎች አለመገዛት፤** ከመስርያ ቤቱ አባሎች በወጡ ምክን ያታዊ መመርያዎች አልገዛም ብሎ አሻፈረኝ ማለት

### ውጤቶች

እነኚህን መመርያዎች መጣስ የሚከተለውን ሊያስከትል ይችላል፤

- የተጀመረው ግንኙነት በአስቸኳይ እንዲቋረጥ ይደረጋል ወይም ከኦ ኤች አር (OHR) ህንጻ እንዲገለሉ ይደረጋሉ።
- ጉዳዮ ይዘጋል ወይም ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል።
- ወደፊት የኦ ኤች አር (OHR) አገልግሎት ማግኘት አለመቻል
- ዛቻ፤ ረብሻ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎች ወስደዋል ተብለው ወደ ህግ አስከባሪዎች መከሰስ

## የልዩ ፍላጎት አቅርቦትለ አካል ጉዳተኞች

አ ኤች አር (OHR) በማእከላይ መንግስትና በ ዲሲ ህግ መሰረት፤ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የልዩ ፍላጎት አቅርቦትለ ያደርጋል።

በማንኛውም ግዜ ማንኛውም አቅርቦት ካስፈልጎት እባኮን ወደ ohr.eeo@dc.gov. ኢሜል ይጻፉ።

የቋንቋ ትርጉም እገዛ ካስፈለገዎ በ ohr.languageaccess@dc.gov. ኢሜል አማካይነት ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ ጥያቄዎች ከለዎ

የደንበኞቻችንን የባህሪ መመሪያዎችን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት እባኮን በሚከተሉት መንገዶች አ ኤች አርን (OHR) ማግኘት ይችላሉ፤

- በኢሜል ወደ ohr@dc.gov ኢሜል ይጻፉ።
- በአካል የሚመጣበት አድራሻ፤ 441 4th Street NW, Suite 570N, Washington, DC 20001
- በስልክ፤ ወደ (202) 727-4559 በመደወል አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።